የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፱
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**33rd Year No.109**
**Addis Ababa 22 octo , 2025**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፻፺፱/፪ሺ፲፰**

**የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ግዥና የሥራ ስምሪት የአሰራር ደንብ**

**ገፅ……………………………………………… ፬ሺ፵፮**

**CONTENT**

**Regulation Number 199/2025**

**A Regulation to Provide for the Procurement of Construction Works and Enrolment Procedure for Contractors**

**Page………………………………….…...….….…. 4046**

## ደንብ ቁጥር ፻፺፱/፪ሺ፲፰

## የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ግዥና የሥራ ስምሪት የአሰራር ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የከተማ ነዋሪ ፍላጎት ለማርካትና የነዋሪውን ችግር ለማቃለል ሰፋፊ የልማት ሥራዎችን ሲያከናውን ከግንባታ ሥራ አፈጻፀም እና ግብዓት አቅርቦት ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮችን እየፈታ በመሄድ በከፍተኛ ሁኔታ ወጪ በመቀነስ በአጭር ጊዜ ውስጥ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ልምድ የተወሰደበት በመሆኑ፤

## Regulation Number 199/2025

## A Regulation to Provide for the Procurement of Construction Works and Enrolment Procedure for Contractors

**WHEREAS,** the Addis Ababa city administration has been addressing several challenges in connection with undertaking construction works and the supply of inputs while implementing massive development activities to alleviate the growing interest of the residents of the city and their problems through reducing government expenditure by taking the experiences gained from the corridor and riverside development works and completing such huge projects in a short period of time;

**የአንዱ ዋጋ**
**Unit price**

**አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭**
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

ይህንኑ ልምድ መነሻ በማድረግ በከተማው አስተዳደር ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች፣ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ላይ ተመስርቶ ድርድር በማድረግ ወጪን በመቀነስ፣ በአጠረ ጊዜ ውስጥ ጥራት ያለው ግንባታ ማስገንባት የሚቻል መሆኑ በመታመኑ፤

የሥራ ተቋራጭ ምልመላ ፍትሃዊ እና ተጠያቂነት ያለበት የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ግዥና የሥራ ስምሪት የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በማጠናቀቅ ለሕዝብ አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህ ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

### ፩.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ግዥና የሥራ ስምሪት የአሰራር ደንብ ቁጥር ፻፺፱/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.<u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ነው፤

**WHEREAS,** based on this experience, it has been believed that through negotiating costs based on single prices and reducing the construction expense of residential houses, corridors, and riverside development projects to be constructed by the city administration and complete quality projects within a short period of time;

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish a fair and accountable selection procedure for contractors and the procurement of construction works and their enrolment that is necessary for the speedy completion of projects and open same for the provision of services to the public;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Powers and Duties of the thereof Proclamation Number 84/2023, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## <u>Part One</u>

## <u>General Provisions</u>

### 1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as: **"Construction Works Procurement and Enrolment Procedure for Contractors Regulation Number 199/2025."**

### 2. <u>Definition</u>

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"City Administration"** means the Addis Ababa city administration;
3. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Specify the Powers and Duties of the thereof Proclamation Number 84/2023;

፬. **“አሠሪ“** ማለት ማንኛውንም የግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም በባለቤትነት የሚከታተልና የሚያስፈጽም ወይም ባለቤት ሲሆን ከአማካሪ ድርጅት ወይም ከሥራ ተቋራጭ ጋር ውል ገብቶ የሚያሰራ አካል ነው፤

፭. **“ሥራ ተቋራጭ”** ማለት ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ በተለያዩ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ የሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፮. **“ነባር ሥራ ተቋራጭ”** ማለት በግንባታ የሥራ መስክ ላይ ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ በግንባታ ሥራ ላይ የቆየ ሥራ ተቋራጭ ነው፤

፯. **“አዲስ ሥራ ተቋራጭ”** ማለት በግንባታ የሥራ መስክ ላይ ከሦስት ዓመት በታች በግንባታ ሥራ ላይ የቆየ ሥራ ተቋራጭ ነው፤

፰. **“ንዑስ ሥራ ተቋራጭ”** ማለት አግባብ ካለው አካል የብቃት ማረጋገጫ በመውሰድ በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ በሥራ ተቋራጭነት ወይም ግብዓት አቅራቢነት የተደራጀ ሆኖ ከዋናው ሥራ ተቋራጭ ሥራ ወስዶ የሚያከናውን ኢንተርፕራይዝ ነው፤

፱. **"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት አግባብ ባለው የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋም በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ደረጃ በግንባታ፣ በግብዓት አቅርቦት ወይም በግንባታ ግብዓት አምራችነት የተደራጀ ነው፤

4. **“Employer”** means any party who undertakes, follows up, and executes any construction **project** either as an owner or as an agent through concluding an agreement with a consulting firm or contractor;

5. **“Contractor”** means an organization that is registered by a legally authorized organ and holds a **competency** certificate as a contractor to engage in various sectors of the construction industry;

6. **“Established Contractor”** means a contractor that has been engaged in the construction **sector** for three years or more;

7. **“New Contractor”** means a contractor that has been engaged in the construction sector for less than three years;

8. **“Sub-Contractor”** means an enterprise with a competency certificate from the relevant **organ** to work as a contractor or input supplier for construction works through taking sub-contracts from the main contractor;

9. **“Enterprise”** means an organ that is organized at the micro, small, and medium level in the areas of **construction**, input supply or production of input supply by the relevant executive organ of the city administration;

፲. **“ቁርጥ ነጠላ ዋጋ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ በየሩብ ዓመቱ እያጠና የሚያቀርበው ወይም በከተማ አስተዳደሩ የቁርጥ ዋጋ እያጠና እንዲተክል የተፈቀደለት ሌላ አስፈጻሚ አካል የሚያወጣው የኮንስትራክሽን ሥራዎች ነጠላ ዋጋ ነው፤

፲፩. **“ባለድርሻ አካላት”** ማለት ከግንባታ ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች፣ የአማካሪ ድርጅቶች፣ ንዑስ ሥራ ተቋራጮች፣ መሠረተ ልማት አቅራቢዎች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ አሰሪ እና አግባብነት ያላቸው የአስፈጻሚ ተቋማት ናቸው፤

፲፪. **“የበላይ ኃላፊ”** ማለት የአሰሪ መሥሪያ ቤቱን በበላይነት የሚመራው ሰው ነው፤

፲፫. **“የሥራ ተቋራጭ ምዝገባ”** ማለት በቁርጥ ነጠላ ዋጋ የግንባታ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ የሥራ ተቋራጭ ወደ ምልመላ ወይም ውድድር ለመግባት በቅድሚያ የሚደረግ ምዝገባ ነው፤

፲፬.**“መዝጋቢ”** ማለት አሰሪው መሥሪያ ቤት ተመዝጋቢ የሥራ ተቋራጭን እንዲመዘግብ የመደበው ሰው ነው፤

፲፭.በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

10. **“Fixed Single Price”** means a fixed single price for construction works that is studied and proposed by the Addis Ababa city administration design and construction bureau quarterly or by another executive body authorized by the city administration to study and fix fixed prices;
11. **“Stakeholders”** means contractors, consulting firms, sub-contractors, infrastructure providers, civic associations, employers, and the relevant executive organs that have direct relationship with the construction work;
12. **“Supervisor”** means a person who is in charge of leading the employer’s office;
13. **“Registration of Contractors”** means a preliminary registration of a contractor who is willing construction works at a fixed single price to engage in recruitment or competition process;
14. **“Registrar”** means a person who is assigned by the employer to register contractors;
15. In this Regulation, any expression in the masculine gender shall apply to the feminine.

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የቤቶች፣ የኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ እና ሌሎች በከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ በልዩ ሁኔታ በሚገነቡ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፬. <u>የደንቡ ዓላማ</u>**

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የሥራ ተቋራጮችን ለመመልመልና የሥራ ስምሪት የሚመራበት ሥርዓት መዘርጋት፤

፪. በቁርጥ ነጠላ ዋጋ በኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ የሚሳተፉ የሥራ ተቋራጮችን ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሠራር ማወዳደርና መለየት፤

፫. የኮንስትራክሽን ሥራዎች በጥራት፣ በተያዘላቸው ጊዜ እና ወጪ እንዲጠናቀቁ ማድረግ፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የሥራ ተቋራጮች ምዝገባና ምልመላ</u>**

**፭. <u>የሥራ ተቋራጮች ምዝገባ ጥሪ</u>**

፩. አሰሪው በከተማው አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ በየሩብ ዓመቱ በሚወጣው የቁርጥ ነጠላ ዋጋ ላይ ተመስርቶ በድርድር ዋጋ ቀንሶ ለመሥራት ፈቃደኛ የሚሆኑ ሥራ ተቋራጮችን ለማሳተፍ በማስታወቂያ፣ በጋዜጣ፣ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በዌብሳይቱ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው አማራጭ ዘዴዎች በመጠቀም ጥሪ ያደርጋል፤

**3. <u>Scope of Application</u>**

This regulation shall be applicable to the housing, corridor and riverside development projects in the Addis Ababa city administration and other construction projects that will be undertaken by the decision of the city administration in special circumstances.

**4. <u>Objective of the Regulation</u>**

The Regulation shall have the following objectives:

1. To establish a procedure for recruiting and employing contractors;
2. To compete and select contractors that will be engaged in a fixed single price construction works in a transparent, fair, and accountable manner;
3. To ensure the completion of construction works with quality, as per the set schedule, and allocated budget.

**<u>Part Two</u>**

**<u>Registration and Recruitment of Contractors</u>**

**5. <u>Call for Contractor's Registration</u>**

1. The employer shall invite contractors who are willing to negotiate, reduce price, and work as per the fixed single price set by the design and construction works bureau of the city administration quarterly through newspapers, television, radio, website, and other relevant alternatives;

፪.የምዝገባ ጊዜው የሚቆየው ለ ፭ (አምስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ብቻ ይሆናል፡፡

**፮. <u>የሥራ ተቋራጭ የምዝገባ መስፈርት</u>**

፩. ለሥራ ተቋራጭ ምዝገባ መሟላት ያለባቸው መረጃዎች፡-

ሀ) የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣
ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣
ሐ) የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣
መ) የገንዘብ ሚኒስቴር ባዘጋጀው የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ስለመመዝገቡ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች በምዝገባው ወቅት የሰነዶቹን ዋናው እና አንድ ቅጂ የሚቀርብ ሆኖ የሥራ ተቋራጩ ማህተምና የሥራ ተቋራጩ የበላይ ኃላፊ ወይም የህጋዊ ተወካይ ፊርማ ሊያርፍባቸው ይገባል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ያልተሟሉ ሰነዶችን ከምልመላ በፊት አንድ ቀን ቀደም ብሎ እንዲያቀርብ ሊደረግ ይችላል፡፡

**፯. <u>የሥራ ተቋራጮች ምዝገባ እና የመዝጋቢው ተግባር</u>**

፩. መዝጋቢው ከተዘረዘሩት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች ዋናውን ከኮፒው ጋር በማመሳከር መረከብ እና መሟላታቸውን በማረጋገጥ ይህን ደንብ ተከትሎ አሰሪው በሚያወጣው ማንዋል መሠረት ይመዘግባል፤

2. The registration period shall only last for 5 consecutive working days.

**6. <u>Requirements for Contractor's Registration</u>**

1. Required Information for the Registration of Contractors
   A. Renewed business license;
   B. Value-added tax registration certificate;
   C. Renewed competence assurance registration certificate;
   D. Provide a certifcate that testifies its registration under the list of suppliers registered by the Ministry of Finance;
2. The original and a copy of the listed documents under Sub-Article (1) of this Article shall be presented during registration and it should bear the seal of the contractor and the signature of the supervisor of the contractor or his representative;
3. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this article, individuals might be asked to submit incomplete documents before one day prior to the recruitment process.

**7. <u>Registration of Contractors and Duties of the Registrar</u>**

1. The registrar shall verify the original and the copy of the documents that are required for registration; make sure that the documents are complete and register contractors based on the manual to be issued by the employer following the issuance of this Regulation;

፪. ሰነድ አሟልቶ ምዝገባውን ላጠናቀቀ ሥራ ተቋራጭ ሠነዱን መግዛት እንደሚችል በማረጋገጫ ቅጽ ፈርሞ ይሰጣል ወይም ሥራ ተቋራጩ ምዝገባ ያካሄደው በኦንላይን ከሆነ የምዝገባ ማረጋገጫ ቁጥር ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

፫. ያልተሟሉ ሰነዶች ለሚያቀርቡ ሥራ ተቋራጮች ሊሟሉ የሚገባቸውን በመዘርዘር ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፬. ምዝገባ የሚከናወነው በአካል በመቅረብ ከሆነ ለማስመዝገብ የሚመጣው ሰው የሥራ ተቋራጩ ሕጋዊ ወኪል ከሆነ የሥራ ተቋራጩ ሠራተኛ ወይም ህጋዊ ወኪል ስለመሆኑ ማስረጃ መቅረቡንና ኮፒው ከሰነዶቹ ጋር መያያዙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፭. የተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮችን መረጃ በሃርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ በማደራጀት መያዝ ይኖርበታል፤

፮. መዝጋቢው ስሙንና ፊርማውን በተመዘገበው መረጃ ላይ በማስቀመጥ ለአሰሪው የበላይ ኃላፊ ምዝገባው እንደተጠናቀቀ በ፭ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፤

፯. መዝጋቢው ተመዝጋቢው የሚያቀርበው ሰነድ ኮፒ ላይ ለምዝገባ ተግባር የተሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ጽሁፍ ማስፈሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፰. መዝጋቢው በምዝገባ ወቅት የሥራ ተቋራጩ የሰጠውን ማስረጃ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት የለበትም፤

2. The registrar will sign a form and give it the contractor to purchase the document when he has fulfilled the necessary documents and finalize the registration process; or if the registration was conducted online, the contractor should come with the registration confirmation number;
3. The registrar should list out the incomplete documents presented by contractors and notify them to complete it;
4. If the registration is done in person, the registrar should make sure that the individual is the legal representative or employee of the contractor and a document is presented for the thereof and its copies are attached;
5. The registrar should organize and maintain the information of the registered contractors with hard and soft copies;
6. The registrar should put his name and signature on the registered information and notify same to the supervisor of the employer within 5 consecutive days upon the completion of the registration process;
7. The registrar should make sure that the copy of the document submitted by the registrant includes a note indicating that the document was only submitted for registration purposes;
8. The registrar should not disclose the evidence provided by the contractor during registration to any other party;

፱. መዝጋቢው አካል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ምዝገባ ያከናውናል፡፡

፰. **<u>በቴክኒክ ሰነድ ላይ ሊያያዙ የሚገባቸው ማስረጃዎች</u>**

፩. አሰሪው ለሚያከናውነው ግንባታ ከሥራ ተቋራጩ የሚያስፈልጉ የባለሙያ ዓይነትና ብዛት በቴክኒክ ሰነዱ ላይ በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

፪. ሥራ ተቋራጩ በአዲስ አበባ ከተማ እና ዙሪያው በተለያዩ ተቋማት ባለፉት አምስት ዓመታት ያከናወናቸውን የግንባታ ሥራዎች አስመልክቶ ስለ ግንባታዎቹ የሚገልጹ ማስረጃዎች፡-

ሀ) የግንባታ ቦታ ርክክብ የተደረገበት ሰነድ፣

ለ) የቅርብ ጊዜ ወይም የመጨረሻ ክፍያ ሰነድ፣

ሐ) ለተጠናቀቁ ግንባታዎች ርክክብ የተፈጸመበት የርክክብ ሰነድ፣

መ) የመልካም ሥራ አፈጻጸም መግለጫ የሚገልጽ የጽሁፍ ሰነድ እና

ሠ) ሲሰራ የነበረውን ፕሮጀክት በተያዘለት በጀት፣ ጊዜና ጥራት ስለማጠናቀቁ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ፤

ከአስገንቢው መስሪያ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፤ ማስረጃውም ትክክለኛ ስለመሆኑ ይረጋገጣል፤

፫. ሥራ ተቋራጩ በተቋሙ ውስጥ ተቀጥረው ስለሚገኙ የምህንድስና፣ ከቴክኒክና ሙያ በደረጃ የተመረቁ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለሙያዎች የትምህርት ማስረጃቸውን፣ የሥራ ልምዳቸውንና የታደሰ የሙያ ምዝገባ መታወቂያ ኮፒ ሰነድ እንደአግባብነቱ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ሰርተፊኬት ማቅረብ አለበት፤

9. The Registrar shall carry out the registration process according to the notice issued under Article 5 of this Regulation.

8. **<u>Evidence to be included in the Technical Documentation</u>**

1. The employer should clearly state in the technical document the type and number of expertise that are required from the contractor for the construction project to be carried out;
2. The contractor should submit the following document regarding the construction works it has carried out for the last five years from the owner from the various institutions in Addis Ababa and its environs; and the submitted document will be authenticated.
   A. Construction site handing over document;
   B. Recent or final payment document;
   C. Handing over document for completed construction;
   D. Written testimony for good performance; and
   E. A written testimony that states the project is completed with quality, as per the set schedule, and allocated budget;
3. The contractor should submit copies of the educational qualifications, work experience, and the renewed professional licence of the engineers, graduates of the technical and vocational institutes, and other professionals that are working in the organization; and their competency assessment assurance certificate, as may be necessary;

፬. ሥራ ተቋራጩ በባለቤትነት የያዛቸውን ማሽኖችና የግንባታ ቁሳቁሶች የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ሰነድ ማቅረብ አለበት፤

፭. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም ሥራ ተቋራጩ ማሽኖችን በኪራይ ያገኘ ሲሆን የማሽን ኪራይ ውል እና የአከራዩ ተቋም በባለቤትነት የያዛቸውን የማሽኖች የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ኮፒ ማቅረብ አለበት፤

፮. ሥራ ተቋራጩ በደረጃው ግዴታ እንዲያሟላ የሚጠበቅበትን የሰው ኃይል የሠራተኞቹን አጠቃላይ ቅጥር በህጋዊ መንገድ መፈጸሙን የሚያሳይ አግባብነት ያለው የታደሰ የቅጥር ውል ሰነድ ማቅረብ አለበት፤

፯. የሥራ ተቋራጩ ያልተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ እያከናወነ የሚገኝ ከሆነ የግንባታ ሥራ ውል ከፈፀመበት አሰሪ መሥሪያ ቤት የተሰጠ ግንባታው የደረሰበትን ደረጃ የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤

፰. ሥራ ተቋራጩ ሌሎች በቴክኒክ ሰነድ ውስጥ ሥራን በጥራት እንደሚሰራ፣ እንዴት በተያዘለት ጊዜ እንደሚያጠናቅቅና በንዑስ ሥራ ተቋራጭነትና ግብዓት በማቅረብ የሚያሰራ መሆኑን የሚያረጋግጡ የተፈረሙ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ማያያዝ ይኖርበታል፤

፱. ሥራ ተቋራጩ በተፈቀደለት ሂሳብ አዋቂ የተረጋገጠ የፋይናንስ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የተሟላ ኦዲት ሪፖርት ማያያዝ ይኖርበታል፤

4. The contractor should provide the original and photocopy of the document that show his ownership of machineries and construction materials;
5. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) of this article, if the contractor has obtained the machineries through lease, he must submit the copies of the machine lease contract and the machineries ownership certificate of the lessor;
6. The contractor should submit a renewed employment contract that shows the employment of the mandatory workforce required for his grade was carried out as per the law;
7. If the contractor is undertaking an unfinished construction work, he should submit a written confirmation from the employer, with whom he has concluded a contract, that states the existing stage of the construction;
8. The contractor should submit a signed written testimony that confirms the way he will carry out the work with the required quality, as per the set period of time, and through hiring sub-contractors and input suppliers with the technical document;
9. The contractor should attach a complete audit report that shows his financial transactions, which was carried out by an authorized accountant;

፲. ሥራ ተቋራጩ ለሥራው የተጠየቀውን ደረጃ ያሟላ መሆን ይኖርበታል፤ ይህን መረጃ ማቅረብ ወይም ማሟላት ያልቻለ ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ከውድድር ውጪ ይሆናል፤

፲፩. ማንኛው ም ያልተጠናቀቀ ግንባታ ያለው ሥራ ተቋራጭ ቀደም ሲል ተዋውሎ የጀመረውን ሥራ ፹፭% (ሰማንያ አምስት በመቶ) ማጠናቀቅ ይኖርበታል፤ ማጠናቀቁን ከአሰሪው መሥሪያ ቤት በሚያቀርበው የጽሁፍ ማስረጃ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፲፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) መሠረት የጀመረውን የግንባታ ሥራ ፹፭% (ሰማንያ አምስት በመቶ) ያላጠናቀቀ ከሆነ በውድድር ውስጥ መሳተፍ አይችልም፤ ያልተጠናቀቀ ሥራ እያለው ይህንን ሳያሳውቅ ከቀረ በማንኛውም ጊዜ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከውድድር ይሰረዛል፤ በህግ ተጠያቂ የሚደረግ መሆኑን በሥራ ተቋራጩ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያለው ደብዳቤ መፃፍ ይኖርበታል፡፡

**፱.<u>የቴክኒክ ሰነድ ሽያጭ ቅድመ ሁኔታዎች እና ሂደት</u>**

፩. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ የቴክኒክ ሰነድ ለመግዛት ከመዝጋቢው ብቁ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ የቴክኒክ ሰነድ ለሚሸጥ አካል ማቅረብ ይኖርበታል፤

፪. ማንኛውም በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ላይ ተመስርቶ በድርድር ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነን የሥራ ተቋራጭ ለመመልመልና ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲያስችል፡-

ሀ) የቁርጥ ነጠላ ዋጋ የተተከለበት የሥራ ዝርዝር፤

10. The contractor should meet the required standards for the work; if any contractor fails to provide or meet this information, he will be disqualified;

11. The contractor with an unfinished construction project should complete 85% (eighty five per cent) of the work that he concluded prior agreement; he should present a written evidence from the employer for doing the thereof;

12. If 85% (eighty five per cent) of the construction work has not been completed according to Sub-Article (11) of this Article, the contractor will not participate in the competition; if the contractor fails to inform such unfinished construction works, he will be disqualified without any circumstances at any time from the competition; and a letter that stated the liability of the contractor as per the law should be written by the supervisor or owner bearing his signature and seal.

**9. <u>Pre-conditions and Process for the Selling of Technical Document</u>**

1. Any contractor should present an evidence from the registrar that he is eligible to purchase a technical document to the one who is selling the thereof;
2. In order to recruit and to ensure the eligibility of a contractor who is willing to negotiate prices based on fixed single price:
   A. List of works for which fixed single price is specified;

ለ) አሰሪው በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ተቋራጩ ሊያሟላ የሚገባቸው መስፈርቶች የሚገልጹ የቴክኒክ መመዘኛ ነጥቦችን የያዘ ሰነድ በማካተት ለተቋራጩ በሽያጭ ይሰጣል፤

፫. ተቋራጩ የተሸጠለት ሰነድ የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ መግዛት ያለበት ሲሆን ይህንንም ለአሰሪው በሚያቀርብለት መተማመኛ ሰነድ ላይ በመፈረም ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሥራ ተቋራጩ መተማመኛ በመፈረም ካላረጋገጠ ሰነዱን ከአሰሪው እንዳልገዛ ተቆጥሮ ከውድድር ውጪ እንዲሆን ይደረጋል፤

፭. ሥራ ተቋራጩ በሰነዱ ላይ እንዲያሟላና የጨረታ ሰነድ መመለሻ ቀን እንዲመልስ የተዘረዘሩትን ሰነዶች በሙሉ አሟልቶ መመለስ ይኖርበታል፤

፮. በቴክኒክ ሰነዱ ላይ እንዲቀርቡ ከተጠየቁት ሰነዶች ውጪ የሥራ ተቋራጩ እንዲያቀርብ አይገደድም፤ ምዘናው የሚካሄደው በቀረበው ሰነድ መመዘኛዎች ብቻ ይሆናል፤

፯. ማንኛውም የሥራ ተቋራጭ በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ላይ ተመስርቶ በድርድር ዋጋ ግንባታውን ለማከናወን ውል ተዋውሎ ወደ ሥራ ከገባ በኋላ ውል በተዋዋለበት ቁርጥ ነጠላ ዋጋ መሰረት ማሻሻያ መጠየቅ አይችልም፤

፰. በቴክኒክ ሰነዱ ላይ እንዲቀርብ የተጠየቀ ማስረጃ የሥራ ተቋራጭ ሰነዱን አሽጎ ካስገባ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፤

B. The employer should include the requirements to be met by the contractor, as per the provision of this Regulation, in the technical assessment criteria for the technical document and avail it for sell;

3. The contractor should verify the document that was sold to him is complete and he must confirm this by signing on the document which he submits to the employer;
4. If the contractor fails to verify the document by signing on it in accordance with Sub-Article (3) of this Article, he shall be presumed not to have purchased the document from the employer and shall be disqualified;
5. The contractor should complete all the listed document according to the requirement and return the bid document by the due date;
6. The contractor shall not be obliged to submit any documents other than the requested ones in the technical document; the evaluation will be conducted solely as per the criteria of the submitted document;
7. Any contractor who has started the construction work by concluding a contract based on the fixed single price through negotiation cannot request for price adjustment as per the fixed single price;
8. Any document presented by the contractor after sealing and submitting the required document according to the technical document will not be accepted;

፱. በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ላይ ተመስርቶ በድርድር ለሚሰሩ ሥራዎች የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡

**፲.<u>የቴክኒክ ሰነድ ሽያጭ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩. ማንኛውም ሰነዱን ለመግዛት የሚመጣ የሥራ ተቋራጭ ከመዝጋቢው የተሰጠውን ብቁ መሆኑን የሚገልፅ ማረጋገጫ ቅጽ መያዙን ያረጋግጣል፤

፪. ሰነዱን የሚገዛው ሥራ ተቋራጭ የተሟላ ሰነድ ስለመግዛቱ የሚገልፅ ቅጽ ላይ በፊርማው እንዲያረጋግጥ ያደርጋል፤

፫. ክፍያ መፈፀሙን በማረጋገጥ የቴክኒክ ሰነዱን ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለድርጅቱ ህጋዊ ወኪል መስጠት ይኖርበታል፤

፬. ሽያጩ በኦንላይን ከሆነ በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱት ሰነዶች ሰለመያያዛቸው ያረጋግጣል፡፡

**፲፩.<u>የሥራ ተቋራጭ ምልመላ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች</u>**

፩. የሥራ ተቋራጮች መመልመያ መስፈርቶች እና መመዘኛ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ በሚደረግ ግምገማ ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ከ፸፭ (ሰባ አምስት) በመቶ በላይ ነጥቦችን ማምጣት ካልቻለ ወደ ውድድር አይገባም፤

፪. ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በግንባታ ሥራ ተቋራጭነት ባከናወናቸው ሥራዎች ላይ በሥራ ተቋራጩ አፈጻጸም ድክመት ምክንያት የግንባታ ውሉ በአስገንቢው የተቋረጠበት ከሆነ በዚህ ውድድር አይካፈልም፤



9. It is not necessary to submit a bid bond for construction works that will be carried out through negotiation based on fixed single price.

**10. <u>Duties and Responsibilities of Technical Document Purchasing Officer</u>**

1. Makes sure that any contractor who wants to buy a document has a form that verifies his eligibility status provided by the registrar;
2. Makes sure that the contractor who is purchasing the document signs on a form stating that he has purchased a complete document;
3. Provides the technical document to the contractor or the legal representative of the organization after confirming that payment has been made;
4. Makes sure that the documents stated under this Article are attached if the purchasing was made online;

**11. <u>Pre-requisites for the Recruitment of Contractors</u>**

1. Any contractor who fails to score 75% of the evaluation based on the criteria and evaluation procedure for the recruitment of contractors will not be legible for the competition;
2. Any contractor who construction work agreement was terminated by the employer due to his poor performance in the past two year will not be legible for the competition;

፫. የሥራ ተቋራጩ በቴክኒክ ሰነዱ ላይ የተጠቀሱትን የሰው ኃይል እና ማሽነሪዎች ሥራውን ሲጀምር ጀምሮ በየደረጃው የሚያቀርብ መሆኑን እና የማያቀርብ ከሆነ በቀጥታ ፕሮጀክቱን የሚነጠቅ መሆኑን የሚያረጋግጥ በሥራ ተቋራጭ ድርጅቱ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያለው ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፲፪.በንዑስ ሥራ ተቋራጭነትና በግብዓት አቅራቢነት ስለማሳተፍ**

፩. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ላይ ተመስርቶ ድርድር በሚከናወኑ ጨረታዎች ላይ ለመሳተፍ ከሚወስደው ግንባታ ላይ እስከ ፳% የሚሆነውን ሥራ ቢያንስ አምስት (፭) እና በላይ ንዑስ ሥራ ተቋራጮችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ በማወዳደር በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ወይም በግብዓት አቅራቢነት እንደሚያሳትፍ ማረጋገጫ በሥራ ተቋራጩ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያረፈበት ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፤ ካላቀረበ ከውድድሩ ውጭ ይሆናል፤

፪. ሥራ ተቋራጩ ንዑስ ሥራ ተቋራጮችን ከአድልዎ በጸዳ መልኩ አወዳድሮ ለመጠቀምና ሥራውን በኃላፊነት ተከታትሎ እንደሚያሰራ በሥራ ተቋራጩ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያረፈበት ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፤

፫. በንዑስ ሥራ ተቋራጭ የሚቀርብ ግብዓትን በሥራ ዝርዝሩ የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ የሚያሟላ ስለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብና በሥራ ዝርዝሩ የተገለጹትን ግብዓት ከንዑስ ሥራ ተቋራጭ በጥራት፣ በዋጋና በጊዜ በማወዳደር ውል ገብቶ ማቅረብ ይኖርበታል፤



3. A contractor should present a confirmation letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the construction firm, regarding the availability of the manpower and machineries that were described on the technical document as of the beginning and every stage of the work and the project will be taken away directly if he fails to do so.

**12. About Participating as Sub-contractors and Input Suppliers**

1. Any contractor participating in a bid to undertake a construction project based on fixed single price negotiation should present a confirmation letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the construction firm, stating the participation of at least five (5) and more contractors as sub-contractors or input suppliers through fair competition for up to 20% of its construction work; if he fails to do so, he will be disqualified from the competition;
2. The contactor should submit a letter of assurance, signed and stamped by the supervisor or owner of the construction firm, stating that the contractor will choose sub-contractors through competition that was free from any bias and engage them in the work and supervise the work in a responsible manner;
3. The contractor should submit an evidence regarding the inputs provided by the sub-contractors meet the quality standards that are specified on the construction work specification and should also enter into a contract with the sub-contractor to supply the inputs stated in the work specification through comparing the quality, price, and with the set time period;

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ እና (፫) የተደነገጉትን ግዴታዎች የግንባታ ውል አካል ይሆናሉ፤

፭. ሥራ ተቋራጩ ከዋና የግንባታ መዋቅራዊ ሥራ ውጭ ባሉ ሥራዎች ንዑስ የሥራ ተቋራጮችን ያሳትፋል፤ የሥራ መስኩ የሥራ ተቋራጩ በሚያቀርበው የሥራ ዝርዝር መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የምልመላ ኮሚቴ ስለማደራጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት እና የድርድር ኮሚቴ መቋቋም

### ፲፫. የምልመላ ኮሚቴ ስለማደራጀት

፩. የሥራ ተቋራጭ ምልመላ የሚካሄደው በአሰሪው ተቋም በሚደራጅ የምልመላ ኮሚቴ ይሆናል፤

፪. ምልመላ ኮሚቴው በመዝጋቢው አካል የተመዘገበውን የሥራ ተቋራጮችን ማስረጃዎች ይረከባል፤

፫. የምልመላ ኮሚቴው ከአባላቱ ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ የሥራ ተቋራጮች ምልመላውን ማከናወን ይችላል፡፡

### ፲፬.የምልመላ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

፩. ኮሚቴው በመዝጋቢው የተመዘገበ የሥራ ተቋራጭ ማስረጃ ይረከባል፤ ይመረምራል፤ የተረከበውን ሰነድ በሚስጥር ይይዛል፤

፪. በምልመላ መስፈርት መሰረት ለተወዳዳሪዎች ነጥብ ይሰጣል፤ ያለፉና የወደቁትን ይለያል፤

፫. ከከፍተኛው ነጥብ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛ ነጥብ ድረስ ያመጡ ሥራ ተቋራጮችን ውጤት በደረጃ ያስቀምጣል፤



4. The obligations that are promulgated under Sub-Article (1), (2), and (3) of this Article shall be part of the construction contract;
5. The contractor should involve sub-contractors in other construction work except the main structural construction work; the specific scope of construction work will be determined as per the list of work provided by the contractor.

## Part Three

## Establishing a Recruitment Committee and Its Duties and Responsibilities and Establishing a Negotiating Committee

### 13. Establishment of Recruitment Committee

1. Recruitment of contractors shall be carried out by a recruitment committee organized by the employing institution;
2. The recruitment committee will receive the documents of the contractors registered by the registrar;
3. The recruitment committee can carry out the recruitment of contractors if two-thirds of its members are present.

### 14. Duties and Responsibilities of the Recruitment Committee

1. The committee shall receive and verify the documents of the contractors that were registered by the registrar; keep the documents in secrecy;
2. Give points for the candidates as per the recruitment criteria; identify the competent and the incompetent ones;
3. Ranks the results of contractors from the highest to the lowest score;

፬. ሥራው በተጠናቀቀ በ፳፬ (ሀያ አራት) ሰዓታት ውስጥ በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የተቋራጮችን የውጤት ደረጃ እና ሌሎች የምልመላ ሠነድ ለአሰሪው ተቋም ይልካል፤

፭. ከምልመላ መስፈርት ውጭ ነጥብ ከሰጠ ወይም ውሳኔ ከወሰነ የኮሚቴው አባላት በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## ፲፭. ስለድርድር ኮሚቴ መቋቋም

የድርድር ኮሚቴ ከከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት የተውጣጡ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩. በከንቲባ የሚሰየም……………… ሰብሳቢ፤
፪. ከቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የሚወከል ……………..………………..…… አባል፤
፫. ከዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ የሚወከል ......……….……….….. አባል፤
፬. ከፋይናንስ ቢሮ የሚወከል ……... አባል፤
፭. ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የሚወከል …..………….……….. አባል፤
፮. ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የሚወከል …………..……….. አባል፤
፯. ከቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የሚወከል .................................................. አባል፤

## ፲፮. የድርድር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው ቁርጥ ነጠላ ዋጋ መነሻ በማድረግ ዋጋን፣ በራሱ የኳሪይ ቦታ ያለው መሆኑ ወይም የግንባታ ተረፈ ምርት ማስወገጃ ቦታ ያለው መሆኑ ወይም ሌሎች አማራጭ የመደራደሪያ ሀሳቦች ላይ ይደራደራል፤ ይወስናል፤ ለአሰሪው መሥሪያ ቤት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

4. The committee shall send the results and other recruitment documents of the contractors, supported by a minute, to the employer within 24 hours after completing the work;
5. The committee members shall be held, individually as well as jointly accountable, if a score was given or a decision was made in contrary to the recruitment criteria.

## 15. Establishment of Negotiating Committee

The Negotiating committee shall consist of the following members comprised from the executive organs of the city administration:

1. An individual assigned by the Mayor …………………………... Chairperson;
2. A representative from the Housing Development and Administration Bureau ………………..……... Member;
3. A representative from the Design and Construction Works Bureau ……………………….…...…. Member;
4. A representative from the Finance Bureau ……………………….… Member;
5. A representative from the Urban Beautification and Green Development Bureau ……………………….… Member;
6. A representative from the Construction Permit and Regulatory Authority …………………………...….. Member;
7. A representative from the Housing Development Corporation..…. Member;

## 16. Duties and Responsibilities of the Negotiating Committee

The committee shall negotiate, based on fixed single price, with the contractor regarding prices, whether the contractor has its own quarry or a dump site for construction debris or on other alternative negotiation ideas; prepares a proposal for decision and submit same to the employer.

**፲፯. ሥራ ተቋራጮች እኩል የሆነ ውጤት ሲያስመዘግቡ የመምረጫ መንገዶች**

፩. እኩል ነጥብ ያላቸው ሥራ ተቋራጮች አዲስ ፈጠራ የታከለበት የግንባታ ቴክኖሎጂ ያቀረበ፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መለየት ካልተቻለ በማጠናቀቂያ ጊዜ መስፈርት ከፍተኛ ነጥብ ባመጣው ቅደም ተከተል መሰረት ይቀመጣሉ፤

፫. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መለየት ካልተቻለ ሥራ ተቋራጮች በዕጣ እንዲለዩ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የሥራ ተቋራጭ የሥራ ሥምሪት

**፲፰. የሥራ ተቋራጮች የሥራ ስምሪት አሰጣጥ**

የተቋራጭ ሥራ ስምሪት በሚከናወንበት ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-

፩. ሥራ ተቋራጮች በአንድ ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ የግንባታ የሥራ መጠን በሥራ ተቋራጭ ብቃት ማረጋገጫ ደረጃ መሠረት ብቻ መሆን አለበት፤

፪. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ በአሰሪው ቀደም ሲል ተዋውሎ የጀመረውን ሥራ ፹፭ በመቶ እና ከዚያ በላይ ያጠናቀቀ ከሆነ ቀሪ ያልተጠናቀቀው ሥራ ሊሰጠው ከሚገባው ሥራ ጋር ተደምሮ የፕሮጀክቱ ብዛትና ዓይነት የሚወሰን ይሆናል፤

፫. የሥራ ተቋራጮች ስምሪት በአሰሪው የሚፈፀም ይሆናል፡፡

**17. Selection Criteria when Contractors get Equal Results**

1. When contractors have got equal results, the contractor that comes up with an innovative construction technology shall be selected;
2. If it is unable to identify the winner based on Sub-Article (1) of this Article, the contractors shall be ranked according to the highest result in the completion criteria;
3. If it is unable to identify the winner based on Sub-Article (1) and (2) of this Article, the contractors shall be identified through lot.

## Part Four

## Placement of Contractors

**18. Undertaking the Placement of Contractors**

The following are the conditions that are taken into account in carrying out the placement of contractors:

1. The construction work that will be awarded to a contractor at one time should only be based on the competence assurance level of the contractor;
2. If any contractor has completed 85 percent and more of the construction work that he had entered an agreement with the employer, the number and type of the project to be awarded for the contractor should be determined through combining same with that of the remaining unfinished construction project;
3. The placement of the contractor shall be carried out by the employer.

## ፲፱. ስለ ሥራ ተቋራጭ ስምሪት

፩. የሥራ ተቋራጭ ሥራ ስምሪት ቡድን የሥራ ስምሪቱን በሚደለድሉበት ወቅት ቃለ ጉባዔዎችን በመያዝ ውይይት ያደርጋሉ፤ በሚያዙ ቃለ ጉባኤዎች ላይ እያንዳንዱ የኮሚቴ አባል መፈረም አለበት፤

፪. ከሥራ ተቋራጭ የምልመላ ኮሚቴ በደረጃ ከከፍተኛው ነጥብ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው ነጥብ ድረስ የተቀመጠውን የተቋራጮች የምልመላ ውጤት ይቀበላል፤

፫. እያንዳንዱን የሥራ ተቋራጭ የምልመላ ኮሚቴ በሰጠው የነጥብ ደረጃ ቅደም ተከተል መሰረት ለድርድር ኮሚቴ መረጃው ይተላለፋል፤

፬. ለአንድ ተቋራጭ በእጁ ያለውን ሥራ ጨምሮ የሚሰጠው ሥራ ለደረጃው በተቀመጠው መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ ብዛቱን ይወስናል፤

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም የሥራው ስፋት ከአንድ ብሎክ ወይም ህንጻ በላይ መሆን የለበትም፤

፮. ከአንድ በላይ ሳይቶች በሚኖሩበት ጊዜ ተቀራራቢ የሆኑ ሳይቶች ውስጥ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

፯. በአንድ ሳይት ውስጥ ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶች የሚሰጡ ከሆነ ፕሮጀክቶቹ ተቀራራቢ እንዲሆኑ በማድረግ ሊሰጥ ይገባል፤

፰. የሥራ ተቋራጭ ስምሪቱን አጠቃላይ ሂደትና ውጤት በሚመለከተው የሥራ ክፍል ተረጋግጦ ለአሰሪው የበላይ ኃላፊ ቀርቦ በማጸደቅ ተቋራጮች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡



## 19. About the Placement of Contractors

1. The contractor placement team should have its own minutes while undertaking the recruitment of contractors; every member of the committee should sign on the minutes;
2. The contractor placement team shall receive the results of the contractors from the recruitment committee that was ranked from the highest to the lowest;
3. The information of every contractor shall be forwarded to the negotiation committee as per the rank given by the recruitment committee;
4. The contractor placement team shall determine the number of projects to be awarded to a contractor through ensuring that the grade of the contractor is in conformity with the job to be awarded, including the remaining projects;
5. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) of this Article, the scope of the work shall not exceed one block or building;
6. When the construction sites are more than one, the committee will ensure that nearby sites are given;
7. If more than one project is there in one site, it should be considered that the projects are adjacent with each other;
8. The contractor placement team shall verify the overall process and result of the placement of the contractors by submitting same to the relevant department and present it the supervisor of the employer for approval; and notify same to the contractors.

### ፳. <u>የሥራ ትስስር ድርሻ መጠን</u>

፩. በማንኛውም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በአሰሪው ለሚገነቡ ግንባታዎች ሥራ ተቋራጮች በአንድ ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ የፕሮጀክት መጠን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ ላይ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፤

፪. በአፈፃፀም ችግር ምክንያት ውለታቸው የሚቋረጡ ፕሮጀክቶች ሲኖሩ ሥራውን ለሌላ ሥራ ተቋራጭ ለመስጠት፡-

ሀ) በምልመላ ወቅት የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው በፕሮጀክት እጥረት ምክንያት ሥራ ሳይሰጣቸው ለቀሩ ሥራ ተቋራጮች በምልመላ ኮሚቴው በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ጥሪ በማድረግ ፈቃደኛ ለሚሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው ድርድር በማድረግ ሊሰጣቸው ይችላል፤

ለ) በተደረገው ጥሪ መሰረት ቀርቦ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ ሥራ ተቋራጭ ካልተገኘ በተመሳሳይ ጨረታ ወቅት ወደ ሥራ ከገቡ ተቋራጮች መሀል የተሻለ አፈፃፀም ላላቸውና ቀሪው ሥራ ከሚፈቀድላቸው የፕሮጀክት መጠን አንፃር ታይቶ ፈቃደኛ ለሆኑ የሥራ ተቋራጮች በድርድር ውጤት መሠረት በመስጠት እንዲሰራ ይደረጋል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) መሰረት ተተኪ ተቋራጭ ማግኘት ካልተቻለ አሰሪው በዚህ ደንብ መሠረት እንደገና ጥሪ አድርጎ ይመለምላል፡፡

### 20. <u>Amount of Work Relation</u>

1. The number of projects to be awarded to contractors at one time for any construction work to be carried out by the employer in any part of the city administration shall be determined as per the provision of Article 19 of this regulation;
2. In order to give the construction work to another contractor, when there are projects whose contracts are terminated due to performance problems:

   A. Construction works might be given to those competent contractors, through negotiation, who have met the criteria during the recruitment process but have not been awarded due to lack of projects shall be invited as per their result ranked by the recruitment committee and if they are willing to do same;

   B. If there is no contractor who is willing to undertake the construction work as per the invitation, the construction work shall be awarded to those contractors who have shown better performance among the contractors who involved in a tender during the same tender period and is willing to carry out the work in through negotiation, confirming the approved number of remaining projects they have at hand;

   C. If it is unable to obtain a replacement contractor according to letter (A) and (B) of Sub-Article (2) of this Article, the employer shall re-call for new contractors and recruit same according to this regulation.

**፳፩.** **<u>የህንጻ እና የጠቅላላ ሥራ ተቋራጮች ከፍተኛ የመጫረቻ ዋጋ በብር</u>**

| ደረጃ | የተቋራጮች የግንባታ መጫረቻ ዋጋ በሚሊየን ብር | |
|---|---|---|
| | የህንጻ ሥራ ተቋራጮች | የጠቅላላ ሥራ ተቋራጮች |
| ፩ | ወሰን የለውም | ወሰን የለውም |
| ፪ | እስከ ፯፻፶ | እስከ ፩.፭ ቢሊዮን |
| ፫ | እስከ ፫፻፶ | እስከ ፯፻ |
| ፬ | እስከ ፪፻ | እስከ ፫፻፶ |
| ፭ | እስከ ፩፻ | እስከ ፻፹ |
| ፮ | እስከ ፵ | እስከ ፸ |
| ፯ | እስከ ፳ | እስከ ፵ |

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የሥራ ተቋራጭ መመልመያ መስፈርት</u>

**፳፪.<u>ጠቅላላ</u>**

አሰሪው ማንኛውም ግንባታ በቁርጥ ነጠላ ዋጋ የተመሰረተ ድርድር ማሰራት ሲፈልግ በዚህ ክፍል የተደነገጉትን መስፈርቶች የሥራ ተቋራጩ እንዲያሟሉ ማድረግ አለበት፡፡

**፳፫. <u>ግንባታዎችን በጥራት ማከናወን</u>**

ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ቀደም ሲል የወሰደውን ግንባታ በጥራት በመሥራት ያጠናቀቀ ከሆነ ፳ (ሀያ) ነጥብ የሚያዝለት ሆኖ ዝርዝር የነጥብ አያያዙ፡-

፩. ሥራ ተቋራጩ ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ እና ዙሪያው ከሰራቸው የግንባታ ሥራዎች ቢያንስ ሁለት ግንባታ የሰራ እና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከ፹፭% (ሰማንያ አምስት) በላይ መሆኑን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ ከአሰሪው መሥሪያ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፤

**21. <u>Highest Bid Price (in Birr) for Building and General Contractors</u>**

| Grade | Contractors' Construction Bid Price (in million birr) | |
|---|---|---|
| | Building Contractors | General Contractors |
| 1 | No limit | no limit |
| 2 | Up to 750 | up to 1.5 billion |
| 3 | Up to 350 | up to 700 |
| 4 | Up to 200 | up to 350 |
| 5 | Up to 100 | up to 180 |
| 6 | Up to 40 | up to 70 |
| 7 | Up to 20 | up to 40 |

## <u>Part Five</u>

## <u>Recruitment Criteria for Contractors</u>

**22. <u>General</u>**

When an employer wants to undertake any construction work based on a fixed single price through negotiation, he should make sure that the contractor meets the requirements set forth in this part.

**23. <u>Carrying out Construction Works with Quality</u>**

If any contractor who completed his previous construction works as per the specified quality, he shall get 20 points and the detailed procedure for the provision of the point shall be:

1. The contractor must submit a written evidence from the employer stating that he has completed at least two construction projects in Addis Ababa and its environs in the past five years and that the project performance of the thereof was more than 85%;

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት የጽሁፍ ማስረጃዎች ከአማካሪ ድርጅት ወይም ከአስገንቢው መስሪያ ቤት የተጻፈ መሆን የሚኖርበት ሆኖ ፬.፯፭ ነጥብ የሚይዝ ይሆናል፤

፫. ሥራ ተቋራጩ ቢያንስ ሶስት የተለያዩ ግንባታዎችን የሰራ እና ከሰራቸው ግንባታዎች ቢያንስ አንዱ የግንባታ ፕሮጀክት ከአዲሱ የግንባታ ፕሮጀክት ጋር ተዛማጅ ወይም ተመሳሳይ ሆኖ ግንባታዎቹን በጥራት ስለማከናወኑ የሚያስረዱ ሰነዶች በአሰሪው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ካቀረበ ፭.፯ ነጥብ ይሰጠዋል፤

፬. የሥራ ተቋራጩ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ፕሮጀክቱን እንዴት እንደሚመራ፣ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉና በአሰሪው መስሪያ ቤት እንዲያሟላ ሲጠየቅ ባለሙያዎችን እንደሚያሳትፍ የሚገልጽ ማስረጃ የሚያቀርብ ፪.፱ ነጥብ ይኖረዋል፤

፭. የሥራ ተቋራጩ ሥራውን በጥራት ለማከናወን የሚከተላቸውን መሰረታዊ ስትራቴጂዎች የሚያቀርብ፣ የሥራ ቦታ ደህንነት የሚጠብቅ መሆኑን ማረጋገጫ የጻፈና በተቋሙ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመ ማህተም ያለው ደብዳቤ ማቅረብ ፩.፱ ነጥብ ይይዛል፤

፮. ሥራ ተቋራጩ በደረጃው እንዲያሟላ የሚጠበቅበትን የሰው ኃይል ያለውና በህጋዊ መንገድ ቅጥር ያከናወነ ወይም ሊቀጥራቸው ያሰባቸውን ባለሙያዎች የሥራ ልምድ፣ የትምህርት ዝግጅትና መታወቂያ እና ፕሮጀክቱን በጥራት ለማከናወን በቴክኒክ ሰነዱ ላይ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ባለሙያዎችን በወቅቱ እንደሚያሟላ በድርጅቱ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያለው ደብዳቤ ማቅረብ ፬.፯፭ ነጥብ ይይዛል፤

2. The written evidence stated under Sub-Article (1) of this Article must be from the consulting firm or the owner and it has 4.75 points;
3. If the contractor submits evidences from the employer that confirm he has carried out three different construction works with quality and at least one project is related to or similar with the new project, he will get 5.7 points;
4. If the contractor submits evidences that state the organizational structure of the firm, how he manages projects, and the involvement of experts and the necessary things requested by the employer to be fulfilled, he will get 2.9 points;
5. If the contractor submits a letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the firm, that states the basic strategies it follows to carry out the construction work with quality and a confirmation for adhering to workplace safety procedures, he will get 1.9 points;
6. If the contractor submits a letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the firm, that confirms he has the required manpower he was expected to fulfil at every stage and hired them legally or the work experience, qualification, and identification card of those professionals he intends to hire and the availability of professionals that are necessary to carry out the project as per the quality standard specified on the technical document, he will get 4.75 points;

፯. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በጥራት በመሥራት የጨረሰ ከሆነ ፳ (ሀያ) በመቶ የሚያዝለት ሆኖ ዝርዝር የነጥብ አያያዙ (ከሶስት ዓመት በታች በግንባታ ሥራው ላይ ለቆዩ አዲስ ሥራ ተቋራጮች)፡-

ሀ) ሥራ ተቋራጩ ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ከሰራቸው የግንባታ ሥራዎች ቢያንስ አንድ ግንባታን የሠራ እና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከ፹፭% (ሰማንያ አምስት) በላይ መሆኑን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ ከአሰሪው መስሪያ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት የጽሁፍ ማስረጃዎች ከአሰሪ መስሪያ ቤቱ ወይም ከቅርንጫፍ ተጽፎ በዋና መስሪያ ቤት የፀደቀ መሆን የሚኖርበት ሆኖ ፬.፸፭ ነጥብ የሚይዝ ይሆናል፤

ሐ) ሥራ ተቋራጩ ቢያንስ ሶስት የተለያዩ ግንባታዎችን የሠራ እና ከሠራቸው ግንባታዎች ቢያንስ አንዱ የግንባታ ፕሮጀክት ከአዲሱ የግንባታ ፕሮጀክት ጋር ተዛማጅ ወይም ተመሳሳይ ሆኖ በጥራት ስለማከናወኑ የሚያስረዱ ሰነዶች በአሰሪው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ካቀረበ ፭.፯ ነጥብ ይሰጠዋል፤

መ) የሥራ ተቋራጩ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ፕሮጀክቱን እንዴት እንደሚመራ፣ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉና በአሰሪው መስሪያ ቤት እንዲያሟላ ሲጠየቅ ባለሙያዎችን እንደሚያሳትፍ የሚገልጽ ማስረጃ የሚያቀርብ ፪.፱ ነጥብ ይኖረዋል፤

7. If any contractor completes his construction works as per the specified quality, he shall get 20 points and the detailed procedure for the provision of the point shall be (for those new contractors who have been on the construction work for less than three years):

A. The contractor must submit an evidence from the employer stating that he has completed at least one construction project in the past three years and that the project performance of the thereof was more than 85%;

B. The written evidence stated under Sub-Article (1) of this Article must be from the employing firm or the branch office and approved by the head office and it has 4.75 points;

C. If the contractor submits evidences from the employer that confirm he has carried out three different construction works with quality and at least one project is related to or similar with the new project, he will get 5.7 points;

D. If the contractor submits evidences that state the organizational structure of the firm, how he manages projects, and the involvement of experts and the necessary things requested by the employer to be fulfilled, he will get 2.9 points;

ሠ) የሥራ ተቋራጩ ሥራውን በጥራት ለማከናወን የሚከተላቸውን መሰረታዊ ስትራቴጂዎች የሚያቀርብ፣ የሥራ ቦታ ደህንነት የሚጠብቅ መሆኑን ማረጋገጫ የጻፈና በተቋሙ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመ ማህተም ያለው ደብዳቤ ማቅረብ ፩.፱ ነጥብ ይይዛል፤

ረ) ሥራ ተቋራጩ በደረጃው እንዲያሟላ የሚጠበቅበትን የሰው ኃይል የቀጠረ ወይም ሊቀጥራቸው ያሰባቸውን ባለሙያዎች ዝርዝር ማስረጃ እና በቴክኒክ ሰነዱ ላይ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ባለሙያዎችን በወቅቱ እንደሚያሟላ በድርጅቱ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያለው ደብዳቤ ካቀረበ ፬.፸፭ ነጥብ ይሰጠዋል፤

፰. አዲስ የተቋቋመ የሥራ ተቋራጭ ከተቋቋመ ሶስት ዓመት ያልሞላው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፫) የተቀመጡት መስፈርቶች የሚይዙትን ነጥብ ፷ በመቶ ይሰጠዋል፡፡

**፳፬. <u>ግንባታዎችን በፍጥነት ከማጠናቀቅ አንጻር</u>**

ማንኛዉም ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በፍጥነት በመሥራት የጨረሰ ከሆነ ፳ በመቶ የሚያዝለት ሆኖ ዝርዝር የነጥብ አያያዙ (ለነባር እና አማራጭ ቴክኖሎጅ ይዘው ለሚቀርቡ ሥራ ተቋራጮች)

E. If the contractor submits a letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the firm, that states the basic strategies it follows to carry out the construction work with quality and a confirmation for adhering to workplace safety procedures, he will get 1.9 points;

F. If the contractor submits a letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the firm, that confirms he has hired the required manpower he was expected to fulfil or the detailed evidence of those professionals he intends to hire and the availability of professionals that are necessary to carry out the project as per the quality standard specified on the technical document, he will get 4.75 points;

8. If the establishment period of the new construction firm is less than three years, it shall get 60 percent of the total points given to the criteria that are specified under Sub-Article (1) and (3) of this Article.

**24. <u>Completing the Construction Works with Speed</u>**

If any contractor completed the construction works with speed, he shall get 20 points and the detailed procedure for the provision of the point shall be (for those experienced contractors and contractors with alternative technologies):

፩. ሥራ ተቋራጩ በደረጃው እንዲያሟላ የሚጠበቅበት ማሽነሪዎች እንደተጠበቁ ሆነው በቴክኒክ ሰነዱ ላይ በተጨማሪነት እንዲቀርቡ የተጠየቁ ማሽነሪዎች በራሱም ወይም በኪራይ የሚያቀርብ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ፲፪ ነጥብ የሚይዝ ይሆናል፤

፪. ባለፉት ፭ (አምስት) ዓመታት ውስጥ ውል ገብቶ የሠራውን ቢያንስ አንድ የግንባታ ሥራ በተያዘለት ጊዜ ገደብ ያጠናቀቀ መሆኑን ማስረጃ የሚያቀርብ ፮ ነጥብ የሚያዝለት ይሆናል፤

፫. ግንባታዎችን በጊዜው ለማጠናቀቅ የሚጠቀምባቸውን ስትራቴጂዎች በጽሁፍ አደራጅቶ ማቅረብ፣ ያስቀመጣቸው ስትራቴጂዎችን ካልፈጸመ በቀጥታ ከሥራ ውጪ የሚያደርግ መሆኑን የማረጋገጫ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ በተቋራጭ ድርጅቱ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያለው ሰነድ የሚያቀርብ ፪ ነጥብ ይያዝለታል፤

፬. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በፍጥነት በመሥራት የጨረሰ ከሆነ ፳ በመቶ የሚያዝለት ሆኖ ዝርዝር የነጥብ አያያዙ (ከሶስት ዓመት በታች በግንባታ ሥራው ላይ ለቆዩ አዲስ ሥራ ተቋራጮች)፡-

1. Notwithstanding the presence of the machineries that are required at every stage, if the contractor submits an evidence that confirms the presence of the required additional machineries as per the technical document by himself or through lease, he shall get 12 points;
2. If a contractor presents an evidence for completing at least one construction work according to the specified period of time with a contract in the last five years, he shall get 6 points;
3. If the contractor submits a letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the firm, that confirms the organization and presentation of written strategies to be implemented for completing the construction works as per the scheduled time and stating the direct termination of contracts if he fails to do so, he shall get 2 points;
4. If any contractor completes his construction works with speed, he shall get 20 points and the detailed procedure for the provision of the point shall be (for those new contractors who have been on the construction work for less than three years):

ሀ) ሥራ ተቋራጩ በደረጃው እንዲያሟላቸው የሚጠበቅበት ማሽነሪዎች እንደተጠበቁ ሆነው በቴክኒክ ሰነዱ ላይ በተጨማሪነት እንዲቀርቡ የተጠየቁ ማሽነሪዎች በራሱም ወይም በኪራይ የሚያቀርብ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ፲፪ ነጥብ የሚይዝ ይሆናል፤

ለ) ባለፉት ፫ ዓመታት ውስጥ ውል ገብቶ የሠራውን ቢያንስ አንድ የግንባታ ሥራ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ያጠናቀቀ መሆኑን ማስረጃ ከአሰሪው መስሪያ ቤት የሚያቀርብ ፮ ነጥብ የሚያዝለት ይሆናል፤

ሐ) ግንባታዎችን በጊዜው ለማጠናቀቅ የሚጠቀምባቸውን ስትራቴጂዎች በጽሁፍ አደራጅቶ ማቅረብ፣ ያስቀመጣቸው ስትራቴጂዎችን ካልፈጸመ በቀጥታ ከሥራ ውጪ የሚያደርግ መሆኑን የማረጋገጫ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ በተቋራጭ ድርጅቱ ኃላፊ ወይም ባለቤት የተፈረመና ማህተም ያለው ሰነድ የሚያቀርብ ፪ ነጥብ ይያዝለታል፤

፭. አዲስ የተቋቋመ የሥራ ተቋራጭ ከተቋቋመ ሶስት ዓመት ያልሞላው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተቀመጡት መስፈርቶች የሚይዙትን ነጥብ ፷ በመቶ ይሰጠዋል፡፡

## ፳፭.ግንባታውን በተያዘለት ወጪ መጨረስ

ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በተያዘለት ወጪ ከጨረሰ ፶ በመቶ የሚያዝለት ሆኖ ዝርዝር የነጥብ አያያዙ፡-



A. Notwithstanding the presence of the machineries that are required at every stage, if the contractor submits an evidence that confirms the presence of the required additional machineries as per the technical document by himself or through lease, he shall get 12 points;

B. If a contractor presents an evidence from the employing office for completing at least one construction work according to the specified period of time with a contract in the last three years, he shall get 6 points;

C. If the contractor submits a letter, signed and stamped by the supervisor or owner of the firm, that confirms the organization and presentation of a written strategy to be implemented for completing the construction works as per the scheduled time and stating the direct termination of contracts if he fails to do so, he shall get 2 points;

5. If the establishment period of the new construction firm is less than three years, it shall get 60 percent of the total points given to the criteria that are specified under Sub-Article (2) and (3) of this Article.

## 25. Completing the Construction Works as per the Allocated Budget

If any contractor completed the construction works according to the allocated budget, he shall get 50 points and the detailed procedure for the provision of the point shall be:

፩. ምንም አይነት የፋይናንስ እጥረት ሊያጋጥመው እንደማይችል ከፋይናንስ ተቋማት ማረጋገጫ ደብዳቤ ያቀረበ ወይም የሥራውን ፴ በመቶ በራሱ የፋይናንስ አቅም መሥራት የሚችል ከሆነ ፴ ከመቶ ነጥብ ይሰጠዋል፤

፪. ተቋራጩ በኦዲተር የተረጋገጠ ትርፋማነቱን የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት የሚያቀርብና በሥራ ውስጥ ያለ መሆኑ ያረጋገጠ ከሆነ ፲ (አስር) ከመቶ ነጥብ ይያዝለታል፤

፫. ባለፉት ፭ ዓመታት ውስጥ በሥራ ተቋራጩ አካውንት ገቢና ወጪ የሆነ ገንዘብ የሚገልጽ ማስረጃ የሚያቀርብ እና የገንዘቡም መጠን በአማካይ የሚወዳደርበትን ፕሮጀክት ያህል ገንዘብ የሚሆን ከሆነ ፲ (አስር) ከመቶ ነጥብ ይያዝለታል፤

፬. አዲስ የተቋቋመ የሥራ ተቋራጭ ከተቋቋመ ሶስት ዓመት ያልሞላው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተቀመጡት መስፈርቶች የሚይዙትን ነጥብ ፷ በመቶ ይሰጠዋል፡፡

## ፳፮.<u>በበጎ ፍቃደኝነት በህብረተሰብ ልማት ተሳትፎ ማድረግ</u>

ማንኛውም የሥራ ተቋራጭ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በበጎ ፍቃደኝነት በማንኛውም የበጎ ፈቃድ ተሳትፎ ካደረገ ፲ (አስር) በመቶ የሚያዝለት ሆኖ ዝርዝር የነጥብ አያያዙ፦

፩. ባለፉት ፭ ዓመታት በበጎ ፍቃድ ተግባር ቢያንስ ሁለት ሥራዎች ላይ መሳተፉን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ ፲ (አስር) ነጥብ ይያዝለታል፤

1. If a contractor submits a letter of assurance from a financial institution that he will not face any forms of financial difficulties or stating he is able to carry out 30 percent of the construction works with his own financial resources, he shall get 30 percent;

2. If the contractor submits a financial report verified by an auditor showing its profitability and that he is currently operational, he shall get 10 percent;

3. If the contractor provides an evidence of the income and expenditure of his financial account in the last 5 years and the amount of money is equal to the average estimated cost of the project for which he is competing, he shall get 10 percent;

4. If the establishment period of the new construction firm is less than three years, it shall get 60 percent of the total points given to the criteria that are specified under Sub-Article (2) and (3) of this Article.

## 26. <u>Voluntary Participation in Community Development Efforts</u>

If any contractor participates in any voluntary service in the Addis Ababa city administration, he shall get 10 percent and the detailed procedure for the provision of the point shall be:

1. If the contractor presents an evidence for his participation in voluntary activities and carrying out at least two works in the past five years, he shall get 10 points;

፪. ባለፉት ፭ ዓመታት በበጎ ፍቃድ ተግባር ቢያንስ አንድ ሥራ ላይ መሳተፉን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ ፭ (አምስት) ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

**፳፯.** **<u>አዎንታዊ ድጋፍ ስለሚደረግበት አግባብ</u>**

በግንባታ ዘርፉ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሴት ሥራ ተቋራጮች ከምዘና ውጤቱ በተጨማሪ ፫(ሦስት) በመቶ አዎንታዊ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለተግባርና ኃላፊነት

**፳፰.** **<u>በአሰሪና ተጠሪ የሆነለት ተቋም መካከል ስለሚኖር ግንኙነት</u>**

ተጠሪ የሆነለት ተቋም በአዋጁ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የደንቡን ተፈጻሚነት በበላይነት ይመራል፤ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፪. ከምዝገባ ጀምሮ ያሉ ተግባራት በአግባቡ ስለመከናወናቸው ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል

፫. ቅሬታዎች ሲቀርቡ በቀረበለት አካል በአግባቡ ስለመመለሳቸው ያረጋግጣል፤

፬. አፈጻጸማቸው የተሻሉ የተባሉና ለማበረታቻ ሽልማት የሚበቁ ተቋራጮችን መረጃ በአግባቡ በመያዝ ከሚመለከታው አካላት ጋር በመሆን የጋራ ያደርጋል፣ ለማበረታቻ ሽልማት ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፭. አግባብ ካለው የከተማ አስተዳሩ አስፈጻሚ ተቋም የተላኩ ኢንተርፕራይዞችን በመቀበል የሥራ ስምሪት እንዲሰጣቸው ለአሰሪው ተቋም ያስተላልፋል፤



2. If the contractor presents an evidence for his participation in voluntary activities and carrying out at least one work in the past five years, he shall get 5 points.

**27.** **<u>Procedure for Affirmative Action</u>**

Women contractors that are engaged in the construction sector shall get 3 points support as an affirmative action in addition to the evaluation result.

## <u>Part Six</u>

## <u>Duties and Responsibilities</u>

**28.** **<u>Relationship between an Employer and Institution Accountable to it</u>**

The Institution, which is accountable to the employer, without prejudice to its power and duties specified under the Proclamation, shall have the following power and duties:

1. Supervises, monitors, and supports the implementation of the Regulation;
2. Follows up and controls the appropriate implementation of the activities starting from registration;
3. Makes sure that complaints are appropriately addressed by the relevant concerned organ;
4. Maintain information properly regarding those contractors who have performed better and fit for incentives and recognition and build a consensus with the relevant organ; makes sure that they are eligible for the incentive and recognition;
5. Accept the enterprises forwarded by the appropriate executive organ of the city government and transfer them to the employer for placement;

፮. ሥራ ተቋራጮች ኢንተርፕራይዞችን የሥራ ስምሪት በአግባቡ እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፯. የባለድርሻ አካላትን በየወቅቱ በመጥራት የግንባታዎችን ነባራዊ ሁኔታ እና እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች ላይ ውይይት ያደርጋል፡፡

**፳፱.የአሰሪው ተግባር እና ኃላፊነት**

አሰሪው በሌላ ሕግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የሥራ ተቋራጮችን ይመዘግባል፣ በመስፈርቱ መሠረት ይመለምላል፤ የሥራ ስምሪት ይሰጣል፤

፪. የሥራ ተቋራጩ ለውድድር ያቀረባቸው ሰነዶች ስለትክክለኛነታቸው በአካል ወርዶ ያረጋግጣል፤

፫. የሥራ ተቋራጮች ስምሪት በህግ አግባብ እየተከናወነ መሆኑን ባለሙያ በመመደብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፬. በአፈጻጸም ችግር ምክንያት ማስጠንቀቂያ የሚሰጣቸውን ጨምሮ የውል መቋረጥ የሚደረግባቸውን የተቋራጮች መረጃ ይይዛል፣ ማስጠንቀቂያውና ውል መቋረጡ በአግባቡ ስለመከናወኑ ያረጋግጣል፤

፭. ውሉ በጠቅላላ የውል ህግና በአስተዳደር የውል ህግ መሰረት ስለመፈጸማቸው ይከታተላል፣ ከውል ውጪ በጊዜና በጥራት የማይከናወኑ ግንባታዎች ላይ አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤



6. Makes sure that contractors are properly carrying out the placement of enterprises;

7. Holds regular discussion with stakeholders regarding the existing condition of the construction projects and the challenges they encounter.

**29. Duties and Responsibilities of the Employer**

The employer, without prejudice to its duties and responsibilities specified under other laws, shall have the following duties and responsibilities:

1. Registers contractors; recruits as per the criteria, and makes placement;

2. Ensures directly that the documents submitted by the contractors for completion are genuine;

3. Follows up and controls that the placement of contractors is being carried out as per the law by assigning a professional;

4. Maintains information on contractors that are subject to contract termination, including those that are given warnings due to performance problems; ensures that the warnings and contract termination are carried out properly;

5. Follows up the implementation of contracts in accordance with the general contract law and the administrative contract law; take or cause the taking of the necessary measures against constructions works that are not completed on time and with quality in contrary to the contract;

፮. አግባብ ካለው የከተማ አስተዳሩ አስፈጻሚ ተቋም የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በመቀበል በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሥራ ስምሪት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፯. ሥራው በተያዘለት ጊዜ፣ ጥራትና ወጪ እየተከናወነ መሆኑን ከአማካሪ ድርጅት፣ ከተቋራጭና ከንዑስ ተቋራጭ ጋር በመሆን ይገመግማል፤ የአፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፰. በቁርጥ ነጠላ ዋጋ የሥራ ተቋራጮችን ለመመልመል የተከናወኑ ተግባራትን እና አጠቃላይ መረጃዎችን አደራጅቶ ይይዛል፤

፱. የድርድር ኮሚቴው የላከለትን የውድድሩን ውጤት በቀረበለት በሦስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ውሳኔውን ሥራ ተቋራጩ እንዲያውቀው በአሰሪው ዌብ ሳይት ወይም አግባብነት ባላቸው የሚዲያ አማራጮች እና በአሰሪው የማስታወቂያ ሠሌዳ ይገለጻል፤

፲፩.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሥራ ተቋራጮቹ በጽሁፍ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

፲፪.ማንኛውም የሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በውል በተያዘለት የጊዜ ገደብና የጥራት ደረጃ መሰረት ማከናወኑ በየጊዜው ያረጋግጣል፤

6. Accept enterprises that are organized by the relevant executive organs of the city government and make sure that they are placed as sub-contractors; follows up the implementation of the thereof;

7. Evaluate the construction project that it is being carried out as per the specified schedule, quality, and cost with the consulting firm, the contractor, and sub-contractors; makes sure that performance reports are submitted regularly;

8. Organizes and maintains the overall information and activities that are carried out to recruit contractors based on fixed single price;

9. Give a decision on the results of the competition submitted by the recruitment committee within three consecutive days after receiving it;

10. The decision made as per Sub-Article (9) of this Article shall be notified for the contractor through the employer’s website or other relevant media alternatives and on the notice board of the employer;

11. Without prejudice to the provision specified under Sub-Article (10) of this Article, the employer will make sure that the contractor receives the decision in writing;

12. Makes sure that any contractor is carrying out the construction project in accordance with the schedule and the required quality.

## ክፍል ሰባት

## ስለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መቋቋም፣ ተግባርና ኃላፊነት እና የአቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

### ፴.የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት የተውጣጡ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩. ከፋይናንስ ቢሮ .......................... ሰብሳቢ፣

፪. ከቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ....... አባል፣

፫. ከዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ ..... አባል፣

፬. ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣ.....አባል፣

፭. ከቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ............ አባል፣

### ፴፩.የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው፡-

፩. በሥራ ተቋራጭ ምዝገባ እና ምልመላ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ ይቀበላል፣

፪. አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው አሰሪው የሰጠውን ውሳኔ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፣

፫. የቀረቡለትን አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

### ፴፪.ስለ ቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

፩. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ምዝገባ የተከለከለ ወይም በምልመላ ውጤት አሰጣጥ ሂደት ወይም ውሳኔ ወይም ሌላ ማንኛውም ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ለአሰሪው የበላይ ኃላፊ ውሳኔው በተሰጠው (፭) (አምስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ ማቅረብ ይችላል፣

## Part Seven

## The Establishment of Complaint Handling Committee, its Duties and Responsibilities, and Submission Procedure

### 30. Establishment of Complaint Handling Committee

The complaint handling committee will consist of the following members from the executive organs of the city government:

1. Finance bureau ………….. chairperson;
2. Housing Development and Management Bureau ………………………. member;
3. Design and Construction Works Bureau ………………………………..member;
4. Construction Permit and Regulatory Authority ……………………. member;
5. Housing Development Corporation…… ……………………..………member;

### 31. Duties and Responsibilities of the Complaint Handling Committee

The complaint handling committee shall:

1. Receives complaints related with the registration and recruitment of contractors;
2. May suspend the decision of the employer temporarily if it deems necessary;
3. Examines the submitted complaints and give decisions

### 32. Complaint Submission Procedure

1. If any contractor who is prohibited to register or dissatisfied with the recruitment procedure or decision or any other decision can submit his complaint to the head of the employer in writing within (5) five consecutive working days after receiving the decision made;

፪. ቅሬታው የደረሰው የአሰሪው የበላይ ኃላፊ ቅሬታው በደረሰው ፫ (ሦስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፤

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ምላሽ ያልተሰጠው ቅሬታ አቅራቢ ምላሽ የሚሰጥበት ጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በ፫ (ሦስት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በዚህ ደንብ መሠረት ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን ያቀርባል፤

፬. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው አቤቱታው በቀረበለት ፫ (ሦስት) ተከታታይ ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭. ኮሚቴው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፤

፮. በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ አቤቱታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፴፫. ስለ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት

፩. ማንኛውም ሰው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል መሆን የሚችለው፡-

ሀ) በሥነ-ምግባርና በሙያ ብቃቱ የተመሰገነ፣

ለ) ከዚህ በፊት በዲስፕሊን ጉድለት ያልተቀጣ፣

ሐ) ለምዘና የተቀመጡ መስፈርቶችንና ሰነዶችን መረዳት የሚያስችል የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ያለው፣

2. The head of the employer who received the complaint shall provide a response within 3 (three) consecutive working days after receiving the thereof;

3. A complainant who is dissatisfied with the decision made as per Sub-Article (2) of this Article or did not get a response can submit his complaint to the Complaint hearing committee that was established according to this Regulation within 3 (three) consecutive working days as of the deadline for submitting a response;

4. The complaint hearing committee shall examine the submitted grievance and give a decision within 3 (three) consecutive days after receiving the thereof;

5. The decision of the committee shall be final;

6. Any contractor who is dissatisfied with the administrative decision can lodge his formal complaint to a relevant court.

## 33. Members of the Complaint Hearing Committee

1. Any individual who will be a member of the complaint handling committee shall be:

   A. Earns respect with his ethical manner and professional competence;

   B. Has no record of disciplinary measures;

   C. Has the educational qualification and work experience to understand the criteria and document set forth for the evaluation;

መ) በመስሪያ ቤቱ ቋሚ ሠራተኛ የሆነ እና ከ ፮ (ስድስት) ወር በላይ ያገለገለ፤ እና

ሠ) ለኮሚቴው አባልነት የሚወከሉ ግለሰቦች በአሰሪው የበላይ ኃላፊ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፤

፪. ከአባላቱ መካከል ቢያንስ ሁለቱ ሴቶች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**<u>፴፬. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስብሰባ እና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሳምንት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ሰብሳቢው በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፫. ሰብሳቢውን ጨምሮ ከግማሽ በላይ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው ይሆናል፤

፬. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሚተላፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፤ ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

፭. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ስብሰባ በስብሰባው የተገኙ አባላት የፈረሙበት ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፡፡



D. A permanent employee of the institution and has served more than 6 (six) months; and

E. The individuals who are assigned for membership should be presented and approved by the head of the employer.

2. At least two of the members should be women.

**<u>34. Meeting and Meeting Procedure of the Complaint Hearing Committee</u>**

1. The complaint hearing committee shall convene once in week;
2. Notwithstanding with Sub-Article (1) of this Article, the chairperson of the complaint hearing committee may call for an extraordinary meeting at any time as may be necessary in the presence of urgent matters;
3. There shall be a quorum where more than half of the members of the complaint hearing committee, including the chairperson are present at a meeting;
4. The decisions of the complaint hearing committee shall be passed by a majority vote; however, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
5. The complaint hearing committee shall keep minutes for its every meeting which is signed by the members that are present at the meeting.

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፭.ቅጣት**

፩. ማንኛውም ሥራ ተቋራጭ ውል ገብቶ በጥራት እና የተያዘለትን ጊዜ ጠብቆ መሄድ ካልቻለና የሥራ አፈጻጸሙ ከጸደቀው የሥራ አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ መርሐ-ግብር እስከ ፲ (አስር) በመቶ ልዩነት ካለው የመጀመሪያ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

፪. በማስጠንቀቂያው መሰረት አስተካክሎና ሥራውን በማፋጠን ወደ ዋናው የውል ጊዜ ውስጥ የማይገባ ከሆነ የሁለተኛ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ማስተካከል ያልቻለ ሥራ ተቋራጭ፡-

ሀ) ሥራው ሊጠናቀቅ የቀረው ከ፲ በመቶ በታች ከሆነ በየቀኑ የፕሮጀክቱን ዋጋ ፩/፩ሺኛ እየተቀጣ የግንባታ ሥራውን ያከናውናል፣

ለ) ቅጣቱ የፕሮጀክቱን ዋጋ ፲ (አስር) በመቶ ድረስ መሄድ ሳያስፈልግ ውሉ እንዲቋረጥ ሊደረግ ይችላል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተደነገገው መሰረት ውሉ ሲቋረጥ ሥራውን የተነጠቀው በውሉ መሠረት ባለመፈጸሙ ከሆነ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በአሰሪው በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ ለሁለት ዓመት አይሳተፍም፣ በውሉ መሰረት ባለመፈጸሙ አግባብነት ባለው በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

## Part Eight

## Miscellaneous Provisions

**35. Penalty**

1. If any contractor with a contract fails to carry out the construction work with quality and the set schedule and his performance deviates up to 10% with that of the approved performance, he will be given with a first level warning;

2. If the contractor fails to correct and expedite the construction work within the schedule of the initial contract, he will be given with a second warning;

3. If a contractor fails to comply with the warnings given under Sub-Articles (1) and (2) of this Article:

   A. carry out the construction work with a fine of 1/1,000 of the project cost per day when 10 percent of the construction is left for completion;

   B. the contract may be terminated without the need to collect 10 percent fine of the project cost;

   C. if the termination of the contract is due to non-compliance of the provision stated under letter (B) of this Sub-Article, the contractor will not participate in any projects that will be carried out by the employer in the city administration for two years; he shall be held accountable as per the relevant laws for his failure not completing the project according to the contract;

መ) በውል አፈጻጸም ክትትል ወቅት ሥራ ተቋራጩ በምዝገባ ጊዜ ለማሟላት ቃል በገባው መሠረት በተሟላ ሁኔታ ሳያሟላ ሲቀር ወይም በውሉ በተገለጸው ፍጥነት ወይም ጥራት እያከናወነ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ወዲያው ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል፣

ሠ) ለውል ማስፈጸሚያ ያስያዘው ገንዘብ ይወረሳል፣

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተራ ፊደል (ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውል ከመቋረጡ በፊት ሥራ ተቋራጩ የተወሰነው ውሳኔ አለአግባብ ነው የሚል ከሆነ በቂ ምክንያት በማስረጃ በማስደገፍ ቅሬታውን ለአሰሪው ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፴፮.ስለተጠያቂነት

፩. ማንኛውም የአሰሪው መስሪያ ቤት ሠራተኛ ፣ ኃላፊ ወይም በዚህ ደንብ የተቋቋመው ኮሚቴ ወይም ሥራ ተቋራጭ የተለየ ጥቅም ለማግኘት ወይም በወዳጅነት ወይም በዝምድና ወይም አግባብ ባልሆነ ሌላ ማንኛውም ግንኙነት በዚህ ደንብ ከተደነገገው ውጭ የሠራ፣ መረጃ የደበቀ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ ያቀረበ ወይም ማንኛውም ከህግ ወጭ የሆነ አሰራር አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ፣ በፍትሐብሄር ህግ ወይም በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ወይም በሁሉም ተጠያቂ ይሆናል፣

፪. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ አፈጻጸም ያሰናከለ ወይም ያስተጓጎለ ከሆነ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

D. if the contractor fails to fulfil the requirements as per the contract at the time of registration or carry out the construction project with quality and speed specified in the contract and such is confirmed during the contract performance monitoring, the contract will be terminated immediately;

E. The cash surety for the contract shall be confiscated.

4. Without prejudice to the provision under letter (C) of Sub-Article (3) of this Article, if the contractor believes that the decision made before the termination of the contract is unfair, he may submit a complaint, supporting it with sufficient evidence, to the employer.

## 36. Accountability

1. Any employee or head of the employing institution or the committee established under this Regulation or contractor who intends to benefit himself or fosters nepotism or works in any inappropriate relationship or conceal information or present forged document or involves in any illegal procedure shall be held accountable as per the relevant penal law, civil law, civil servants' Proclamation or with all.
2. Any person who impedes or obstructs the implementation of this Regulation shall be held accountable with the relevant laws.

**፴፯.<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፴፰.<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ይህንን ደንብ የሚቃረን የከተማው ካቢኔ ያወጣው ደንብ፣ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፴፱.<u>መመሪያ ስለማውጣት</u>**

ካቢኔው ለዚህ ደንብ ማስፈጸሚያ የሚሆን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፵.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፰**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**



**37. <u>Duty to Cooperate</u>**

Any individual shall be duty bound to cooperate to execute this Regulation.

**38. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any Regulation issued by the cabinet of the city or any directive or customary practices which are inconsistent with this Regulation shall have no effect.

**39. <u>Power to Issue Directives</u>**

The cabinet may issue directives for the implementation of this Regulation.

**40. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 22nd day of October 2025.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of October 2025.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**